# WHERE TO?

In the project „Where to?", organised by different Goethe-Instituts worldwide, authors and intellectuals from almost 40 countries were given a questionnaire on refuge and migration. The sources of inspiration were questionnaires by Swiss writer Max Frisch, drafted in his diaries between 1966 and 1971. The answers from around the world vary greatly, reflecting the authors' personal experiences but also the situation in different countries – while at the same time showing the complexity and interconnection of this topic.
The poster exhibition presents a compilation of selected questions and answers. The photographs are from the series "Ça va waka" by Algerian born photographer Nassim Rouchiche. They document the place taken by illegal immigrants in the society in which Nassim Rouchiche lives.


Project idea and realization: Goethe-Institut Addis Ababa
Text compilation: Daniel Worku
Photographs: Nassim Rouchiche
Design: Brook Getachew
Website: www.goethe.de/whereto

# ወደ የት?

‹‹ወደ የት?›› በሚል ስያሜ በዓለም ላይ ባሉ የተለያዩ ጎተ- ኢኒስቲትዩቶች ውስጥ በተዘጋጀ ፕሮጀክት ላይ 40 የሚሆኑ አገሮች ደራሲያንና ምሁራን በስደተኛ እና ስደት ላይ ለቀረቡ መጠይቆች መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡ የፕሮጀክቱ መነሻ ታዋቂው የስዊዝ ደራሲ የነበረው ማክስ ፍሪሽ እ.አ.አ በ1966 እና 1971 መካከል በግል ማስታወሻው ላይ ስለ ጓደኝነት፣ ትዳር፣ ገንዘብ ወይም ሞት ያነሳቸው አጫጭርና ጠቅለል ያሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የደራሲያኑን የግል ልምድ ያንፀባረቁ፣ ሆኖም ግን በተለያዩ ሀገሮች ያሉትን ሁኔታዎች ያገናዘቡ - በዚያው ልክ ደግሞ የጉዳዩን ውስብስብነትና ተያያዥነትን የፈተሹ ከዓለም ዙሪያ የተሰበሰቡት እነዚህ መልሶች በጣም የተለያዩ ናቸው፡፡
እዚህ የምትመለከቷቸው ፖስተሮች አርባ የሚጠጉ ደራሲያንና ምሁራን ለተጠየቁት 21 ጥያቄዎች ከሰጧቸው መልሶች የተውጣጡትን ናቸው፡፡ በፖስተሩ ላይ የሚታዩት ፎቶዎች የፎቶ ባለሙያው፣ አልጄሪያዊው ናሲም ራውቺች "Ça va waka" በሚል ስያሜ ከሚያወጣቸው ተከታታይ ፎቶዎች የተወሰዱ ናቸው፡፡ ፎቶዎቹ ናሲም ራውቺች በሚኖርበት አካባቢ ማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩ ህገ ወጥ ስደተኞች የያዟቸውን ቦታዎች ሰንደው የሚያቆዩ ናቸው፡፡

የፕሮጀክቱ ሃሳብ አመንጪና አስፈፃሚ፣ ጎተ-ኢንስቲትዩት አዲስ አበባ
ጽሑፎች መረጣና ትርጉም፣ ዳንኤል ወርቁ
ፎቶ፣ ናሲም ራውቺች
ዲዛይን፣ ብሩክ ጌታቸው
ድረ-ገፅ፣ www.goethe.de/whereto

GOETHE
INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.



# WHAT DOES THE TERM REFUGEE MEAN TO YOU?

## ስደተኛ የሚለው ቃል ለእርስዎ ያለው ትርጉም ምንድን ነው?

**Here, we say; „The seasons do not chase birds away; birds chase the seasons away“. Unfortunately, a refugee does not tame the inclement seasons but the seasons rather chase him away. The most unfortunate refugees are refugees in their own country. They have been nicknamed „displaced persons“. Here, we say, „Is a bird afraid of its own nest still a bird? Is this nest still a nest?“**

እኛ ሀገር እንዲህ የሚል አባባል አለ፤ “ወቅቶች ወፎችን አያሳድዷቸውም፣ ወፎች ወቅቶችን እንጂ” እንደ አለመታደል ሆኖ ስደተኛ ወቅቶችን አያሳድድም ይልቅ ወቅቶች ናቸው እሱን የሚያሳድዱት። ፍፁም የተረገሙ ስደቶኞች በገዛ ሀገራቸው የሚሰደዱ ናቸው። ቅፅል ስም ተሰጥቷቸዋል። “ተፈናቃዮች” የሚል። እኛ ሀገር እንዲህ የሚል አባባል አለን፤ “የራሱን ጎጆ የሚፈራ ወፍ ወፍ ነውን? ጎጆውስ ጎጆ ነውን?


**Lye M. Yoka, Democratic Republic of the Congo, Writer and University teacher**

ሌ ኤም. ዮካዲ፣ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኮንጎ፣ ጸሐፊ እና የዩኒቨርሲቲ መምህር

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT

Sprache. Kultur. Deutschland.



# WHAT DOES THE TERM REFUGEE MEAN TO YOU?

## ስደተኛ የሚለው ቃል ለእርስዎ ያለው ትርጉም ምንድን ነው?

**A lost soul.**
ማረፊያ ያጣ ነፍስ

**Yasmina Khadra, Algeria / France, Pseudonym of Algerian writer Mohammed Moulessehoul, today living in France.**
ያስሚን ካድራ፣ አልጀሪያ / ፈረንሳይ፣ መሐመድ ሞልሶል፣ ያስሚን ካድራ በሚል የብዕር ስም የሚታወቅ ደራሲ፡፡

**A man who has nowhere to return to.**
መድረሻ ቢስ!

**Dubravka Stojanovic, Serbia, Historian**
ዱብራቭካ ስታኖቪክ፣ ሰርቢያ፣ የታሪክ ባለሞያ

**The dream of finding memory in another place. The dream of belonging to a legitimate elsewhere.**
ትዝታን ሌላ ቦታ የመፈለግ ህልም። በሌላ ቦታ ህጋዊ ተቀባይነት የማግኘት ህልም።

**Colum McCann, Ireland / USA, Writer and Journalist**
ኮለም ሜካን፣ አየርላንድ / ዩ ኤስ ኤ፣ ጸሐፊና ጋዜጠኛ

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

© Nassim Rouchiche

# WHAT DOES THE TERM REFUGEE MEAN TO YOU?

# ስደተኛ የሚለው ቃል ለእርስዎ ያለው ትርጉም ምንድን ነው?

**A refugee is a human being whose personal tragedy has become a public commodity in a strange land. A person who is on show for everyone. Answerable to all. Dependent on anyone. Protected by no one.**

ስደተኛ ማለት በእንግዳ ሀገር የግል ሰቆቃው የህዝብ ሸቀጥ የሚሆን ሰው ማለት ነው። ለሁሉ ሰው ትርኢት፣ በሁሉ ሰው የሚጠየቅ፣ ሁሉ ሰው ላይ ጥገኛ የሆነ እና በማንም ጥበቃ የማያገኝ ማለት ነው።

**Ruwanthie de Chickera, Sri Lanka, Theatre and Film producer**
ሩዋንቲ ዴ ቺከራ፣ ሲሪላንካ፣ የቲያትርና ፊልም አዘጋጅ

**It means someone who is seeking refuge, and is, or should be, protected by ancient and modern covenants of the offer of shelter and protection from danger. Homer's Odyssey, the founding epic of tragic homelessness, situates the rights of the suppliant as sacred: Zeus is the 'protector of strangers', patron of a universal code of conduct in which altruism is essentially a matter of self-interest – you feed and clothe and house the outsider because one day you may need the same assistance. Thus, exceptionalism, or contracting out of this mutual law of hospitality, is ultimately a form of self-harm.**

በዘመናዊውም ሆነ በጥንታዊው ስምምነቶች መሰረት መጠጊያ የሚያነፈንፍ እና ከለላ እና መጠጊያ ሊሰጠው፣ ከአደጋ ሊታደጉት የሚገባ ሰው ማለት ነው። ስለ አሳዛኝ ቤት አልባነት የሚተርከው የጀግንነት ረጅም ግጥማዊ ትረካ መሰረት የሆነው የሆሜሩ ኦዴሲ፣ የምንዱባንን ጥያቄ የቅድስና ቦታ ሰጥቶታል። ዜዉስ "የፀጉረ ልውጦች ጠባቂ፣ መከታ ነበር።" ለጋስነት፣ ቸርነት ነግ በኔ ነው በሚል ስሜት፣ የተቸገረን መመገብ፣ ማልበስ እና መጠለያ መስጠት የግል ተነሳሽነት የነበረበት የሁለንተናዊው ዓለም የስነ ምግባር መርህ ደጋፊ ነበር። ሰለሆነም ከዚህ የጋርዮሽ ህግ ማፈንገጥ በስተመጨረሻ ራስን በራስ የመጉዳት መንገድ ነው።

**Frances Stonor Saunders, Great Britain, Historian and Writer.**
ፍራንሲስ ስቱነር ሳውንደርስ፣ታላቋ ብሪታንያ፣ የታሪክ ባለሙያና ፀሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# WHAT DOES THE TERM REFUGEE MEAN TO YOU?

## ስደተኛ የሚለው ቃል ለእርስዎ ያለው ትርጉም ምንድን ነው?

ስደተኛ ማለት ከጨለማ ውስጥ ብርሃን ፍለጋ የሚሮጥ ማለት ነው። ያጣውን ሰዋዊ ማንነት ለመመለስ የሚንቀዠቀዥ ማለት ነው። በእርግጥ የሰው ልጅ መሆኑን እና በዚህ ምድር ላይ የመኖር መብት እንዳለው የሚያረጋግጥበት ቦታ የሚፈልግ ማለት ነው። እንዲያም ሆኖ ይህን  መብት ላማግኘት የመኖር መብት የሚሰጡት ፖለቲከኞችን እና ሌሎች አካላት ላይ ህልውናው የተንጠለጠለ ሰው ማለት ነው።

**A refugee is someone who runs out of darkness in search of light. She/he is a person looking for a place to bring back their lost human elements, it is a person who is looking for a place to prove that he/she is a human being and have the right to live on earth. Well, but this all depends on the attitude of the political powers and the generosity and cordiality of others to guarantee her/his right to live.**

**Daniel Worku Kassa, Ethiopia, Author, Translator, Critic and Filmmaker**
ዳንኤል ወርቁ  ካሳ፣ ኢትዮጲያ፣ ደራሲ፣ ተርጓሚ፣ ሃያሲ፣ ፊልም ሰሪ

**Refugees are people who don't even have the right to have rights anymore. Every refugee is a mirror of our failed policies, a sign that there is something deeply rotten in our contemporary world if such a thing as a refugee is still possible.**

ስደተኞች ማለት፤ መብት እንዲኖራቸው እንኳ መብት የሌላቸው ሰዎች ናቸው። እያንዳንዱ ስደተኛ የወደቁት ፖሊሲዎቻችን ማሳያ ናቸው። በዛሬው አለማችን ውስጥ የሆነ ስር ሰዶ የበሰበሰ ነገር መኖር ምልክት፣ እስካሁንም ድረስ እንደ ስደት ያሉ ነገሮች መኖራቸው ነው።

**Srećko Horvat, Croatia, Philosopher**
ስሬኮ ሆርቫት፣ ክሮሺያ፣ ፈላስፋ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# WHAT DOES THE TERM REFUGEE MEAN TO YOU?

## ስደተኛ የሚለው ቃል ለእርስዎ ያለው ትርጉም ምንድን ነው?

The leader of the rearguard in Troy, Aeneas, is an impressive refugee. He crosses the Mediterranean Sea. Troy's misfortune is glued to the soles of his feet. This way, although he brings his amorousness to the beautiful queen Dido, he brings little luck. He founds Rome. Rome destroys the Greek city of Corinth. This refugee is the messenger of long-term revenge for what the Greeks did to Troy.

An example of the opposite is my grandmother's grandmother, Caroline Louise Granier, a refugee from France. In the southern Harz Mountains, she found her German husband. Later, they carefully read Goethe's "Hermann und Dorothea", the mirror image of their own fate. I would not be here today without this refugee woman. By the way, Huguenots – refugees just like this woman – were the engine propelling Germany forward by more than 50 years. These are strokes of luck. I associate the term "refugee"with "luck"and with "bringer of bad tidings"and thus with a large number of tales and novels.

በትሮይ የደጀን ጦር መሪ አኔስ አስገራሚ ስደተኛ ነው። የሜዲትራንያንን ባህር አቋረጠ። የትሮይ መጥፎ እድል ከጫማው ሶል ጋር ተጣብቆ ነበር። ምንም እንኳ ለውቧ ንግስት ዲዶ የፍቅር ቂጤማ ይዞ ቢመጣም፣ ያመጣው እድል ግን ትንሽ ነበር፡፡ ሮምን አገኘ፣ ሮም የግሪክን ከተማ ኮሪንቶስን ደመሰሰች። ይህ ስደተኛ ግሪኮች በትሮይ ላይ ላደረሱት የረጅም ጊዜ በቀል መልእክተኛ ነው።

የዚህ ምሳሌ ተቃራኒ ከፈረንሳይ የመጣችው ስደተኛ የአያቴ አያት ካሮሊነ ሉዊዘ ግሬኒየር ናት። በደቡባዊ የሃርስ ተራሮች መሀከል ጀርመናዊ ባልዋን አገኘችው። ቆይተው የራሳቸው ህይወት እጣ ፈንታ ነፀብራቅ የሆነውን  የጎተን "ኸርማን እና ዶርቲ"ን በጥንቃቄ አነበቡ።  ይህች ስደተኛ ሴት ባትኖር ኖሮ እኔ ዛሬ እዚህ አልገኝም ነበር። በነገራችን ላይ ሁጉዌኖትዝ ስደተኞች ልክ እንደዚህች ሴት ጀርመንን ከሀምሳ አመታት በላይ ወደፊት ያሽከረከሩ ሞተሮች ነበሩ። እነዚህ የእድል ምቶች ናቸው። እኔ "ስደተኛ" የሚለውን ቃል  ከ "እድል"፣"እድለኛ ስደተኞች እና "እግረ ደረቅ ስደተኞች" ጋር አስተሳስረዋለሁ። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከብዙ ተረቶች እና ረጅም ልቦለዶች ጋር።

**Alexander Kluge, Germany, Writer, Film Maker and Producer.**
አሌክሳንደር ክሉገ፣ ጀርመን፣ ደራሲ፣ የፊልም ባለሙያ እና ፕሮድዩሰር

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# IS THERE A NATURAL RIGHT TO ASYLUM?
# ጥገኝነት ተፈጥሯዊ መብት ነው?

**Here, we say, “Bozoba Esala ngando: Akimi Mbula akweyi na Ebale” “Poor caiman fleeing from getting wet in the pouring rain, and finding refuge in the river”. There are no conditions to be free. There are no conditions to be a free man or a free woman among free men and women.**

እኛ ዘንድ አንድ አባባል አለ፣ “ምስኪን አዞ በዝናብ ላለመበስበስ ሲሸሽ ወንዝ ውስጥ መጠለያ አገኘ”
ነፃ ለመሆን ገደቦች የሉም፡፡ ነፃ በሆኑ ወንዶችና ሴቶች መካከል፣ ነፃ ወንድ፣ ነፃ ሴት የሚባል ጉዳይ የለም፡፡

**Lye M. Yoka, Democratic Republic of the Congo, Writer and University teacher**
ሌ ኤም. ዮካ፣ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኮንጎ፣ ጸሐፊ እና የዩኒቨርሲቲ መምህር

**Yes. And if not for other reasons, then only because we are all refugees, in the end. Europe, for instance, as we know it today, is the result of numerous wanderings of entire populations in the course of history, triggered by wars, epidemics, poverty, natural disasters, ethnic, political, religious, cultural persecution. It is the ethical duty of humans to protect their kind from danger, whatever that danger may be, not least because the so-called developed countries, and especially Europe and the United States, are directly responsible for a large part of the refugees in the world, because of the economic disorganization which they encouraged and continue to encourage with their behavior which is aimed at geopolitical hegemony.**

አዎ። ሌላ ምክንያት እንኳ ባይኖር፣ እኛ ሁላችን በስተመጨረሻ ስደተኞች በመሆናችን ብቻ። አውሮፓ ለምሳሌ ዛሬ እንደምናውቀው ይህን መልኩን ያገኘው በታሪክ ውስጥ በነበረው ቁጥር ስፍር በሌላቸው፣ ምክንያታቸው፣ ጦርነት፣ ወረርሽኝ፣ ድህነት፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ የዘር፣ የፖለቲካ፣ የኃይማኖት፣ የባህል ግድያዎች፣ በሆኑ ከፍተኛ የህዝቦች እንቅስቃሴዎች እና ዝውውሮች ነው። የሰው ልጅ የራሱን አምሳያ፣ አደጋው ምንም አይነት ይሁን ከአደጋ መጠበቅ ስነምግባራዊ ሃላፊነት ነው። ምክንያቱም እነዚህ የበለፀጉ የሚባሉት ሀገሮች፣ በተለይ አውሮፓ እና ሰሜን አሜሪካ በዓለም ላለው አብዛኛው ስደተኛ ቀጥተኛ ሃላፊነት አለባቸው። ምክንያቱም የፖለቲካ እና የስነምህዳር የበላይነትን ትክረቱ ባደረገው ባህርያቸው እነሱ የሚያበረታቱት እና አሁንም ማበረታታቸውን ባላቋረጡት የተዘበራረቀው ምጣኔ ሃብት ነው።

**Luiz Ruffato, Brasil, Writer**
ሉዊዝ ሩፋቶ፣ ብራዚል፣ ጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE
INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# IS THERE A NATURAL RIGHT TO ASYLUM?
# ጥገኝነት ተፈጥሯዊ መብት ነው?

**I am very skeptical about the idea of a natural right, and certainly am not a supporter of arguing in favor of a right by appealing to its naturalnessRights are postulated, and in the best case they are recognized. The right to asylum has a long tradition from the ancient world and other cultures, and is also at the base of the image (traditionally sacred) of hospitality.**


እኔ የተፈጥሮ መብት የሚለው አስተሳሰብ ላይ ጥርጣሬ አለኝ፡፡ በእርግጠኝነት አዛኝነት ተፈጥሮአዊ ነው ብለው ተቀብለው ሽንጣቸውን ገትረው ከሚከራከሩት አውቅና ካገኙት ወገን አይደለሁም። የስደተኛነት መብት ከጥንታዊ  ዓለም እና ሌሎች ባህሎች ጀምሮ ረጅም ልምድ ያለው ነው። እናም ከመሰረቱ (በባህል የተቀደሰ) የመልካም አቀባበልን ምስል የያዘ ነው።

**Milagros del Corral, Spain, Librarian**
ሚላግሮሰ ደ ኮራል፣ ስፔን፣ የቤተ መጻሕፍት ባለሙያ

**Of course, He must observe and respect all the laws, the rules of that country. We have a wonderful saying: “When you‘re in a foreign country, you have to put on your head the hat worn by those living there.”**

እንዴታ! ግን የዛን ሀገር ህግ እና ስርዓት አክባሪ መሆን አለበት። እኛ በጣም ግሩም የሆነ አባባል አለን። “በውጭ ሃገር ስትኖር በእዚያ ሀገር የሚኖሩ ሰዎች የሚያዘወትሩትን ኮፍያ ማድረግ አለብህ” የሚል።

**Temur Butikashvili  Georgia Filmmaker**
ቴሙር ቡቲካሽቪሊ፣ ጆርጂያ፣ የፊልም ባለሙያ




© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# HOW MUCH “HOME” DO YOU NEED?

## ምን ያህል መኖሪያ ያስፈልግዎታል?



**Every single one of us need the whole world. We need the whole world in order to be fully human and humane. People must be able to move as they have moved across the continents since life on earth came into existence.**

እያንዳንዳችን መላውን ዓለም እንፈልጋለን። የተሟላና ሰብዓዊ ሰው ለመሆን ነው መላውን ዓለም የምንፈልገው። የሰው ልጆች ህይወት በምድር ላይ ከተዘራች ጀምሮ ያደርጉት እንደነበረው ገደብ የለሽ እንቅስቃሴ፣ መንቀሳቀስ መቻል አለባቸው።

**Antjie Krog, South Africa, Poet, Writer, Journalist**
አንትጄይ ክሮግ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ገጣሚ፣ ጸሐፊ፣ ጋዜጠኛ


**Home, as Mahfouz says, is not where you were born, but where all your attempts to escape cease. So home is a trap, and we should all try to need as little “home” as we can.**

መኖሪያ፣ ማህፉዝ እንዳለው የተወለድክበት ቦታ አይደለም ነገር ግን ለማምለጥ የምታደርጋቸው ሙከራዎች የሚቆሙበት ቦታ ነው፡፡ ከመቆም ለማምለጥ የተንፈራገጥክበት እንጂ። ስለሆነም መኖሪያ ወጥመድ ነው፡፡ እናም ሁላችንም በተቻለ መጠን ሚጢጢ መኖሪያ እንድንመኝ መጣጣር ይኖርብናል።

**Aman Sethi, India, Journalist and Writer**
አማን ሴቲ፣ ህንድ፣ ጋዜጠኛና ጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.



# HOW MUCH “HOME” DO YOU NEED?

## ምን ያህል መኖሪያ ያስፈልግዎታል?

I feel that the entire world is my homeland and in that sense, I need a big house, a huge one. I am an aspiring mad man at the thought that the entire world is my homeland. If someone will place a border in front of me, I will look into his eyes and tell him: you are a foreigner in this homeland.

ዓለም በሙሉ መኖሪያ ቤቴ እንደሆነ ይሰማኛል። በዛ ስሜት ግዙፍ ቤት እፈልጋለሁ፣ እጅግ ግዙፍ። ዓለም በሙሉ የኔ ቤት ነው ብዬ የማስብ ጉጉ እብድ ሰው ነኝ። አንድ ሰው ከፊት ለፊቴ ድንበር ሊያቆም ቢፈልግ አይን አይኑን እያየሁ፣ “አንተ በዚህ ምድር ላይ ያለህ የሌላ ዓለም ሰው ነህ” እለዋለሁ።

**Erri de Luca, Italy, Writer**
ኢሪ ደ ሉቻ፣ ጣሊያን፣ ጸሐፊ

Ever since I turned to my inner refuge, my only homeland has been the one within me. This is where I am able to set its boundaries, to decide how strong it is going to be at a certain point in time and I can make sure that it will not leave me like the previous one.

ውስጤ ወዳለው ስደተኛ ፊቴን ካዞርኩ ጀምሮ ብቸኛው የትውልድ ሃገሬ ማለት በውስጤ ያለው ነው። እዚህ ነው ድንበሮቹን መከለል፣ በጊዜ ውስጥ የሆነ ነጥብ ላይ ምን ያህል ጥብቅ መሆን እንደሚቻል መወሰን፣ እናም እንደ ቀድሞው ቤቴ ጥሎኝ እንደማይሄድ እርግጠኛ መሆን የምችለው።

**Dubravka Stojanovic, Serbia, Historian**
ዱብራቭካ ስታኖቪክ፣ ሰርቢያ፣ የታሪክ ባለሞያ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# HOW MUCH “HOME” DO YOU NEED?

## ምን ያህል መኖሪያ ያስፈልግዎታል?

**A lot. I am always on the lookout, but I know it exists in different places, both in space as in time. On the other hand, I manage very well without homelands.**

ብዙ። እኔ ሁልጊዜ ፍለጋ ላይ ነኝ፡፡ ነገር ግን በሁለቱም በጊዜ እና በቦታ በተለያዩ ቦታዎች እንደሚኖር አውቃለሁ። በሌላ መንገድ ግን ይኸው ያለ ትውልድ ሀገር በጣም በተሳካ ሁኔታ እየኖርኩ ነው።

**Hans van den Brink, Netherland, Writer and Journalist**
ሃንስ ቫን ደ ብሪክ፣ ኔዘርላንድስ፣ ጸሐፊና ጋዜጠኛ

**My memories are my home.**
ትዝታዎቼ ናቸው የኔ መኖሪያ።

**Sirpa Kähkönen, Finland, Autorin und Kolumnistin**
ሲርፓ ኬህኮነን፣ ፊንላንድ፣ ደራሲና ዓምደኛ

**Home is not a physical place. It’s a feeling.**
መኖሪያ ቁሳዊ ቦታ አይደለም፡፡ ስሜት ነው።

**Ruwanthie de Chickera, Sri Lanka, Theatre and Film producer**
ሩዋንቲ ዴ ቺከራ፣ ሲሪላንካ፣ የቲያትርና ፊልም አዘጋጅ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# HOW MUCH “HOME” DO YOU NEED?

## ምን ያህል መኖሪያ ያስፈልግዎታል?



**Actually only one and that is planet Earth. The individual parts of the body of Mother Earth may have different names: The belly might be China, the back might be Russia, the right calf might be Germany, the left thumb Switzerland, the sole of the right foot Iraq, the left one Iran, and so on. But all of this belongs to the body of the earth, planet Earth. And it belongs to you, to me, to her: to each African gatherer, to each Chukchi hunter. She produced us all, nourished us and will admit us again into her big, kind belly when our time on earth will come to an end. For this reason, she is our mother, and for this reason, we call her Mother Earth. And this one and only Mother Earth is our big, shared home!**

በእርግጥ አንድ ነው የምፈልገው፣ ያችም ፕላኔት መሬት ናት። የተለያዩ የእናት መሬት አካላት የተለያየ ስም ሊኖራቸው ይችላል። ሆድዋ ቻይና፣ ጀርባዋ ምናልባት ሩስያ፣ ቀኝ ጎንዋ ምናልባት ጀርመን፣ ግራ ጎንዋ ምናልባት ስዊዘርላንድ፣ የቀኝ እግሯ የውስጡ እግር ኢራቅ፣ የግራዋ ኢራን፣ እያለ ይቀጥላል። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ የመሬት አካላት ናቸው፤ የፕላኔት መሬት። እናም ያንቺ፣ ያንተ፣ የኔም ናቸው። ለእያንዳንዱ አፍሪካዊ እረኛ፣ ለቹክቺ አዳኝ። ሁላችንንም ወደ እዚህ አምጥታናለች፣ መግባናለች፡ ፡ በዚህች ምድር ላይ የምንኖርበት ጊዜ ሲያበቃም በድጋሚ ወደ ሰፊው እና ቸሩ ማህፀንዋ መልሳ ታስገባናለች። በእነዚህ ምክንያቶች ሳቢያ እናታችን ናት፤ በዚህ ምክንያት እናት መሬት እንላታለን። እናም ይህች አንድ እና ብቸኛ እናት መሬት ትልቋ እና የምንጋራት መኖሪያችን ናት።

**Galsan Tschinag, Mongolia, Writer and tribal chief**
ጋልሳን ቲሺናግ፣ ሞንጎሊያ፣ ጸሐፊና የጎሳ አለቃ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.



# IS THERE A NATURAL RIGHT TO ASYLUM?

## ጥገኝነት ተፈጥሯዊ መብት ነው?

አዎ፣ በማንኛውም ሃገርም ሆነ በተባበሩት መንግስታት ህግጋት ውስጥ አልተካተተ የሆናል እንጂ ጥገኝነት የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ መብት ነው። ልክ እንደ ወፎች እና አንስሳት፡ ፡ መሬት፣ ደቡብ አፍሪካም ሆነ አላስካ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ ቢጫ ሆነ ነጭ ሆኖ ይወለድ የሰው ልጆች በሙሉ መኖሪያ ነች። መሬት ላይ እስከ ተወለድክ ድረስ በዚች ምድር ላይ የመኖር መብት አለህ። እስቲ ወፎችን ተመልከቷቸው። ወፎች እንደልብ የመንቀሳቀስ እና በሄዱበት ጥገኝነት ማግኘት ተፈጥሮአዊ እንደሆነ ለማሳየት ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

**Yes, it may not be written in any countries' or United Nations' laws but asylum is a natural right of human beings, like birds and animals. Earth is a common place for human beings. Born in South Africa or Alaska or born black, brown, yellow or white since you are born on earth you have got every right to live on this earth. Look at the birds, birds are a good example of a natural right and exercise of the freedom to emigrate.**


**Daniel Worku Kassa, Ethiopia, Author, Translator, Critic and Filmmaker**
ዳንኤል ወርቁ ካሳ፣ ኢትዮጲያ፣ ደራሲ፣ ተርጓሚ፣ ሃያሲ፣ ፊልም ሰሪ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# IS FLIGHT FROM POVERTY LESS LEGITIMATE THAN FLIGHT FROM WAR OR POLITICAL OPPRESSION?

## በድህነት ምክንያት መሰደድ ተቀባይነቱ በጦርነት ወይም በፖለቲካ ጭቆና ምክንያት ከመሰደድ ያነሰ ይሆን?



There are so many forms of poverty in the world, as there are refugees that are just not named that way, aren't there? For example, isn't the contemporary European youngster departing his or her shores to escape economic difficulties and the lack of a future to find shelter and refuge in Angola and Mozambique not an economic refugee too?
To be human is to move, to leave a toxic environment, as with any organism, in order to find solidarity, community and air to breathe. I do not believe it is a question of 'legitimacy', that is political sophistry, but of human values and valuing.

ገና ስያሜው ያልተሰጣቸው ስደቶኞች እንዳሉ ሁሉ፣ በአለማችን ብዙ አይነት የድህነት ገፅታዎች አሉ፡፡ የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ድህነቶች አሉ። አሉ አይደል? ለምሳሌ ዛሬ ካለችው አውሮፓ ወጣቶች በኢኮኖሚ ችግሮች እና በአማራጭ እጦት ምክንያት ወደ አንጎላ እና ሞዛምቢክ መጠለያ ፍለጋ የሚሰደዱት የኢኮኖሚ ስደተኞች አይደሉምን?
ሰው መሆን ማለት እንደልብ መንቀሳቀስ መቻል ማለት ነው። እንደ ማንኛውም ህይወት ያለው ፍጥረት ፣ ወዳጃዊነትን፣ ማህበረሰብን እና የሚተነፍሱትን ንፁህ አየር ፍለጋ የተበከለን አካባቢ ጥሎ መሄድ። በሰው ልጅነት ክብር እና እሴቶች አንፃር ይህ የተገቢነት/ህጋዊነት ጥያቄ ነው የሚል እምነት የለኝም። ያ ፖለቲካዊ ማደናበሪያ ነው።

**Yvonne Adhiambo Owuor, Kenia, Writer**
ይቮነ አዲሃምቦ አውር፣ ኬንያ፣ ጸሐፊ


**Whoever flees poverty seeks fortune; whoever flees war only seeks to live.**

በድህነት ሳቢያ የሚሰደድ የተሻለ ሃብት ፍለጋ ነው፣ በጦርነት ሳቢያ የሚሰደድ ግን መኖርን ብቻ ነው የሚፈልገው።

**Yasmina Khadra, Algeria / France, Pseudonym of Algerian writer Mohammed Moulessehoul, today living in France.**
ያስሚን ካድራ፣ አልጀሪያ / ፈረንሳይ፣ መሐመድ ሞልሶል፣ ያስሚን ካድራ በሚል የብዕር ስም የሚታወቅ ደራሲ፡፡

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.



DO YOU THINK YOU WILL EVER BE A REFUGEE?
አንድ ቀን እሰደዳለሁ ብለው ያስባሉ?
Nothing is impossible.
አይሆንም የሚባል ነገር የለም።
Galsan Tschinag, Mongolia, Writer and tribal chief
ጋልሳን ቲሺናግ፣ ሞንጎሊያ፣ ጸሐፊና የጎሳ አለቃ
Yes, unfortunately, I can imagine that without further ado, I am thinking about it every day – for political reasons.
እንደ አለመታደል ሆኖ አዎ አስባለሁ። ብዙም ማሰብ ሳያስፈልገኝ ያንን አልማለሁ። በየቀኑ አስበዋለሁ ፖለቲካዊ በሆነ ምክንያት።
Frances Stonor Saunders, Great Britain, Historian and Writer.
ፍራንሲስ ስቱነር ሳውንደርስ፣ ታላቋ ብሪታንያ፣ የታሪክ ባለሙያና ፀሐፊ
No, I do not think so, and if I will be I would seek refuge on Iceland.
አይመስለኝም፣ መሰደድ ካለብኝ ግን አይስላንድውስጥ ነው ጥገኝነት የምጠይቀው።
Jørgen Lorentzen, Norway, Film producer and author.
ዮርጋን ላረንቲዝ፣ ኖርዌይ፣ የፊልም ፕሮዲውሰር እና ደራሲ
GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.
© Nassim Rouchiche

# DO YOU THINK YOU WILL EVER BE A REFUGEE?

## አንድ ቀን እሰደዳለሁ ብለው ያስባሉ?

**No, I do not think I will ever be one. I am a public figure in Lithuania. Therefore, if my country, God forbid, were in trouble, I would act in a decent way. In case of war, I would not flee. I would never abandon my country, should war or a similar social calamity break out. If my country slides into a tyranny, which would be as awful as being invaded, then I would have to remain a dissenting voice.**

አላስብም። በፍፁም እኔ ከስተኞች አንዱ እሆናለሁ ብዬ አላስብም። እኔ ሊቱዊንያ ውስጥ ተደማጭነት ያለኝ ታዋቂ ግለሰብ ነኝ። እና እግዜአብሔር አያድርገው እና አገሬ ላይ ችግር ቢፈጠር በተገቢው መንገድ እንቅስቃሴ አደርጋለሁ። ጦርነት ቢቀሰቀስ አገሬን ጥዬ አልሸሽም። ፈፅሞ አገሬን ጥዬ አልሄድም፣ ጦርነትም ሆነ ተመሳሳይ ማህበራዊ ቀውስ ቢፈጠርም እንኳን፡፡ አገሬ መራርነቱ ከውጭ ሃይል ከመወረር በማይተናነሰው በአንባገነን መዳፍ ውስጥ ከወደቀች የተቃውሞ ድምፅ ሆኛ እዛው እቀራለሁ።

**Leonidas Donskis, Lithuania, Philosopher, Historian, Writer**

ሌዎኒዳስ ዶንስኪ፣ ሊቱዊንያ፣ ፈላስፋ፣የታሪክ ምሁር፣ ጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT

Sprache. Kultur. Deutschland.

# DO YOU THINK YOU WILL EVER BE A REFUGEE?

## አንድ ቀን እሰደዳለሁ ብለው ያስባሉ?

I do not believe that any one is able to categorically exclude becoming a refugee at some point in time. The world is strange and changes rapidly, especially when one lives in a third world country. As far as Brazil is concerned, politics is making trouble right now. We are but one step removed from the end of being a state that is under the rule of law – ideological groups are attacking each other, and what is most inconspicuous is intolerance. Also the Christian-Evangelical fundamentalists who are gaining influence to a disproportionate extent are characterized by intolerance. Our democracy is still young, meaning it is vulnerable, and the elite in Brazil is very attached to the privileges it has been enjoying ever since. So one can never exclude that I, too, might have to flee to another country
in case of political regression. But the point is, as I said at the beginning, that one never is a refugee out of one's own free will but always due to a lack of alternatives.

ማንም ሰው ከእለታት አንድ ቀን ስደተኛ ላልሆን እችላለሁ ብሎ ራሱን መነጠል አይችልም። ዓለም እንግዳ ናት፣ በፍጥነት ትለዋወጣለች። በተለይ በሶስተኛው ዓለም ለሚኖር ሰው። ብራዚልን በተመለከተ አሁን የፖለቲካ ትኩሳት እየተፈጠረ ነው። በህግ እና በሰርዓት የሚመራ መንግስት መሆናችን ሊያበቃለት አንድ እርምጃ ብቻ ነው የቀረው። የተለያዩ ቡድኖች በአለመለካት ልዩነት እርስበርስ ይሻኮታሉ። በጣም አስፈላጊው ነገር መቻቻል ነበር። ዲሞክሪያሲያችን ገና ወጣት ነው፣ ይህ ማለት አደጋ አለው ማለት ነው። ብራዚል  ውስጥ ደግሞ በእውቀት የላቁትና በሃብት የበለፀጉት  ገና ከመጀመሪያው እያጣጣሙት ካለው ጥቅማ ጥቅም ጋር ተቆራኝተዋል። ስለሆነ አንድ ሰው እኔም አንድ ቀን አየከፋ በሚመጣው የፖለቲካ ዝቅጠት ሳቢያ ልሰደድ እችላለሁ ብሎ አለማሰብ አይችልም። ነገር ግን ዋናው ነገር  መጀመሪያ ላይ እንዳልኩት፣ አንድ ሰው በምንም መልኩ በገዛ ፍቃዱ አይሰደድም አማራጭ ከማጣት አንጂ።

**Luiz Ruffato,Brasil, Writer**
ሉዊዝ ሩፋቶ፣ ብራዚል፣ ጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# CAN YOU IMAGINE A WORLD WITHOUT REFUGEES?

# ዓለምን ያለስደተኛ ማሰብ ይችላሉ?

**I wouldn’t want to, it’s like trying to imagine a system ‘so perfect that no one will need to be good’ (T S Eliot). Beware utopia.**

አልፈልግም። ልክ ፍፁም የሆነ እና ‘ማንም ሰው መልካም እንዲሆን የማይጠበቅበት ስርዓትን’ እንደመመኘት ማለት ነው። (ቲ ኤስ አልየት)። ተምኔታዊ ከሆነ ፍፁም ዓለም ተጠንቀቁ።

**Frances Stonor Saunders, Great Britain, Historian and Writer.**
ፍራንሲስ ስቱነር ሳውንደርስ፣ ታላቋ ብሪታንያ፣ የታሪክ ባለሙያና ፀሐፊ

**Unfortunately no. As long as there is global capitalism which is, on the one hand, based on free circulation and brutal accumulation of goods, and on the other, on restricted circulation of humans, there will be refugees. As long as there is a system in which capital is worth more than any human, there will be people who will on a daily basis be transformed into “human waste“**

እንደአለመታደል ሆኖ አልችልም። ባንድ በኩል አስቀያሚ የሃብት ማግበስበስ እና በነፃ ኡደት ላይ መሰረቱን ያደረገ ግሎባል ካፒታሊዝም፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጆች የተገደበ እንቅስቃሴ እስካለ ድረስ ስደተኝነት ይኖራል። ንብረት ከማንኛውም የሰው ልጅ በላይ ሚዛን የሚደፋበት ስርዓት እስካለ ድረስ፣ በየቀኑ ወደ የሰው ቆሻሻነት የሚሸጋገሩ ሰዎች ይኖራሉ።

**Srećko Horvat, Croatia,Philosopher**
ስሬኮ ሆርቫት፣ ክሮሺያ፣ ፈላስፋ

በጭራሽ! ዓለም ይህንቅርጿን ያገኘችው በስደተኞች ነው። ሃብታም ከሆኑት የአውሮፓ ሃገራት የተሰደዱ ስደተኞች ዓለምን የለወጧት፣ ስደተኝነታቸውን በተቀበሏቸው ሀገሮች ውስጥ ሆነው በነፃነት ማሰብ በመቻላቸው ነው። ለሰው ልጅ ነፃነት መሰረታዊ ነገር ነው። ሰዎች ጦርነትን ሽሽት፣ ድህነትን ሽሽት፣ የፖለቲካ እንግልትን ሽሽት፣ የተፈጥሮ አደጋን ሽሽት ብቻ አይደለም የሚሰደዱት፣ አዕምሮአቸውን በሙሉ አቅሙ ለማሰራት የሚችሉበትቦታ ፍለጋ ጭምር ይሰደዳሉ።

**No not at all. The world is shaped by refugees. Even refugees from very rich places like Europe have had the chance to think properly, and to change the world from within the countries that absorbed them. Freedom is very essential to human beings. People are not seeking asylum only because of poverty, war, political operations or environmental changes, there are refugees fleeing to seek places where they can fully exploit their intellectual abilities.**

**Daniel Worku Kassa, Ethiopia, Author, Translator, Critic and Filmmaker**
ዳንኤል ወርቁ ካሳ፣ ኢትዮጲያ፣ደራሲ፣ ተርጓሚ፣ ሃያሲ፣ ፊልም ሰሪ

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

© Nassim Rouchiche

# CAN YOU IMAGINE A WORLD WITHOUT REFUGEES?

## ዓለምን ያለስደተኛ ማሰብ ይችላሉ?

**I neither believe in miracles nor in utopias. There will be wars, famine and natural disasters also in the future. So, unfortunately, I cannot imagine a world without refugees.**

እኔ በተዓምርም፣ ተምኔታዊ በሆነ ፍፁም ዓለምም አላምንም። ወደፊትም ጦርነቶች ይኖራሉ፣ ድርቅ የኖራል፣ የተፈጥሮ አደጋ ይኖራል። ስለዚህ እንደ አለመታደል ሆኖ ከስደተኛ ነፃ የሆነ ዓለም ለማለም አልችልም።

**Petros Markaris, Greece, Writer and Translator**
ጴጥሮስ ማርካሪስ፣ ግሪክ፣ ጸሐፊና ተርጓሚ

**Only through the suicide of humankind through some colossal catastrophe can I imagine a few survivors withdrawing into themselves and in their own place. Since the beginning of the Holy Scriptures the Deity has been telling humankind to multiply and spread over the faces of the Earth. We are a wandering and vagrant species, we look at the stellar space looking for a new Earth.**

የሰው ልጆችን በሙሉ ከምድረ ገፅ የሚያጠፋ ግዙፍ የተፈጥሮ አደጋ ተከስቶ ጥቂት የተረፉ ሰዎች በራሳቸው መሬት ላይ ተረጋግተው ይኖራሉ ብዬ መገመት እችላለሁ። ከቅዱሳን መፃህፍት ጀምሮ አምላክ የሰው ልጆች እንዲባዙና ምድርን እንዲሞሏት ተናግሯል፡፡ እኛ ተንከራታችና እና ዘዋሪ ፍጡሮች ነን። ህዋ ውስጥ አዲስ ምድር እየፈለግን እኮ ነው።

**Erri de Luca, Italy, Writer**
ኤሪ ደ ሉቻ፣ ጣሊያን፣ ፀሐፊ

**No. I do not believe that there will be an end to this saga.**
አላስብም። የዚህ የጅብደኝነት ታሪክ ማብቂያ ይኖረዋል ብዬ አላምንም።

**Hans van den Brink, Netherland, Writer and Journalist**
ሃንስ ቫን ደ ብሪክ፣ ኔዘርላንድስ፣ ጸሐፊና ጋዜጠኛ

**Yes. But I know I‘m dreaming.**
አዎ፣ ግን እያለምኩ እንደሆነ አውቃለሁ።

**Geneviève Brisac, France, Writer; Short Stories, Theatre Plays, Film Scripts and Children’s Books.**
ጀኔቬ ባዛክ፣ ፈረንሳይ፣ የአጫጭር ታሪኮች፣ የፊልም፣ የህፃናት መጻሕፍት ፀሐፊና ፀሐፊ ተውኔት

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# CAN YOU IMAGINE A WORLD WITHOUT REFUGEES?

## ዓለምን ያለስደተኛ ማሰብ ይችላሉ?

**Yes, I believe that one day humanity will live in a world without refugees. Man is eventually an intelligent being. A day will come when people will understand that wars, conflicts and racism may lead to the destruction of all of us since the lethal weapons and destruction weapons are improving. I do believe that one day we will learn to understand that we all belong to one race and one nation and that we all populate one homeland, which is the Earth. In such a future world, there will not be starving refugees who wander destitute in hostile fields**

አዎ አንድ ቀን የሰው ልጅ ስደተኛ አልባ በሆነ ዓለም ውስጥ እንደሚኖር አስባለሁ። ሰው ዞሮ ዞሮ ብሩህ አእምሮ ያለው ፍጡር ነው። ጅምላ ጨራሽ የሆኑ መሳሪያዎች እየተሻሻሉ እስከተሰሩ ድረስ፣ ጦርነቶች፣ ግጭቶች፣ ዘረኝነት መጥፊያችን እንደሆኑ ሰዎች የሚረዱበት ቀን ይመጣል። አንድ ቀን ሁላችንም አንድ ዘር፣ አንድ ህዝብ እንደሆን እና ሁላችንም አንድ የትውልድ ቦታ እንዳለን ያችም መሬት እንደሆነች የምንማርበት ጊዜ እንደሚመጣ አምናለሁ። በዚህ መፃኢ ዓለም የተራቡ እና በጠላት ክልል ውስጥ የሚንከራተቱ ምስኪን ስደተኞች አይኖሩም።

**Sami Michael,Israel,Author**
ሳሚ ሚካኤል፣ እስራኤል፣ ደራሲ


**No. Of course, I would like to imagine a world without military conflicts, famine and natural disasters but such a vision would be too far from realty. Another question would be if we could imagine a world in which the term “refugee” would have lost its meaning – in so far as this term is connected to territorial nation states which can accept or refuse refugees as they wish. Possibly, we can imagine such a world as a positive perspective of development – such as Kant’s vision of eternal peace in which states are connected by the right of hospitality.**

አይ! በእርግጥ ወታደራዊ ግጭቶች፣ ረሃብ እና የተፈጥሮ አደጋዎች የሌሉባት ዓለም መመኘት እፈልጋለሁ፤ እንዲህ አይነት ምኞት ግን ከእውነታው አጅግ በጣም የራቀ ነው። ሌላው ጥያቄ ሊሆን የሚችለው “ስደተኛ” የሚለው አባባል ትርጉሙን የሚያጣበትን ዓለም ይመጣል ብላችሁ ታስባላችሁ ወይ ነው፡፡ እስካሁን ይህ ቃል የተያያዘው ድንበር ካላቸው እና ለመፍቀድም ለመንሳትም መብት ካላቸው መንግታት ጋር ነው። ምናልባት ለእድገት ከሚኖር ቀና የሆነ አስተሳሰብ ተነስተን እንዲህ አይነቱን ዓለም ማሰብ የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል፤ ልክ እንደ ኢማኑኤል ካንት እሳቤ መንግስታት በእንግዳ ተቀባይነት መብት የሚተሳሰሩበትን ዘላለማዊ ሰላም የመሰለ።

**Ivars Ijabs, Latvia, Political Scientist, Correspondent**
ኢቫርስ ኢጃብስ፣ላቲቪያ፣ የፖለቲካ ሊቅ፣ ዘጋቢ ጋዜጠኛ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.



# WHEN DOES ONE CEASE TO BE A REFUGEE?

## ሰው መሰደዱን የሚያቆመው መቼ ነው?

አንድ ሰው ነፃነትን ሲያጣጥም፣ በነፃነት የማሰብ፣ ለማህበረሰቡ ማድረግ የሚችለውን እንደ ልቡ ሲያደርግ፣ ስጋት እና ሰቆቃ የሌለበት ህይወት መኖር ሲጀምር፣ አንድ ሰው እንደ ማህበረሰቡ አባል ሰው መሆኑ እውቅና የሚያገኝበት ቦታ ሲኖረው፣ የማህበረሰቡ አባል መሆኑ ሲሰማው እና እንደ ሰው ልጅ መንቀሳቀስ ሲጀምር ነው።

**It is when a person feels the taste of freedom: free to think, free to move and contribute what s/he can to the society. It is when one lives a life without fear and terror. It is when one has a recognizable place as a member of a community or believes she or he is accepted, and starts to act as a human being.**

**Daniel Worku Kassa, Ethiopia, Author, Translator, Critic and Filmmaker**
ዳንኤል ወርቁ ካሳ፣ ኢትዮጲያ፣ ደራሲ፣ ተርጓሚ፣ ሃያሲ፣ ፊልም ሰሪ

**When one finds a home that feels natural. When one is allowed to remember what you lost.**

እንድ ሰው ልክ እንደ ትውልድ ስፍራው ስሜት የሚሰጠው መኖሪያ ሲያገኝ። አንድ ሰው ያጣቸውን ነገሮች እንዲያስታውስ መብት ሲሰጠው።


**Colum McCann, Ireland / USA, writer and journalist**
ኮለም ሜካን፣ አየርላንድ / ዩ ኤስ ኤ፣ ጸሐፊና ጋዜጠኛ

**When all national boundaries have disappeared.**
ድንበሮች በሙሉ ሲጠፉ።

**Choi Zin A, Korea, Playwright and Theatre Director**
ቾይ ዚን ኤ፣ ኮርያ፣ ጸሐፊ ተውኔት እና አዘጋጅ

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

© Nassim Rouchiche



# WHEN DOES ONE CEASE TO BE A REFUGEE?

## ሰው መሰደዱን የሚያቆመው መቼ ነው?

When one can choose not to tell ones' story in order to justify one's presence.

አንድ ሰው በሌላው በሌላው ዘንድ ህልውናውን ለማረጋጋጥ ሲል ፣ታሪኩን መናገር አላስፈላጊ ሲሆን።

**Ruwanthie de Chickera, Sri Lanka, Theatre and Film producer**
ሩዋንረቲ ዴ ቺከራ፣ ሲሪላንካ፣ የቲያትርና ፊልም አዘጋጅ

**In some areas of the heart and as far as the sensation on the skin is concerned, never. But one escapes the "fate of a refugee"where new ground emerges. Traditionally speaking, this would mean: When one builds a house, plants a tree, has a child. In the 21st century, this is more complex: Where is the chance to get established on new soil to be offered, in concrete individual cases? I practically stop being a refugee when I found a new home. When I become a patriot in a new way. I can be a patriot for holy books, concerning my profession and, as mentioned, when I build a new house.**

የልብ ውስጥን እና ከውጪ የሚመጣ ስሜትን እስከተመለከተ ድረስ በፍፁም። ነገር ግን የሰው ልጅ አዲስ ቦታ ላይ ኑሮ ሲመሰርት "የስደተኝነት እጣ ፈንታ"ን ማምለጥ ይችላል፡፡ ይህ ማለት በዘልማድ፣ አንድ ሰው ቤት ሲሰራ፣ ዛፍ ሲተክል፣ ልጅ ሲወልድ ማለት ነው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ይህ የበለጠ ውስብስብ ነው። ተጨባጭ የሆኑ ግለሰባዊ ሁኔታዎችን ብናይ የት ነው በሚሰጠው አዲስ ቦታ ላይ የመረጋጋት እድሉ ያለው? እኔ ስደተኛ መሆኔን በተግባር የማቆመው አዲስ ቤት ሳገኝ፣ በአዲስ መልክ ሀገር ወዳድ ስሆን ነው፡፡ ለቅዱሳን መጻሕፍት፣ ለሙያዬ እና ከላይ እንዳልኩት አዲስ ቤት ስገነባ አርበኛ መሆን እችላለሁ።

**Alexander Kluge, Germany, Writer, Film Maker and Producer.**
አሌክሳንደር ክሉገ፣ ጀርመን፣ ደራሲ፣ ፊልም ሰራተኛ እና ፕሮዲውሰር

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# ARE THERE PRIVILEGED REFUGEES IN YOUR COUNTRY, I.E. REFUGEES THAT ARE MORE WELCOME THAN OTHERS? IF YES: WHY?

## በሀገርዎ ልዩ ጥቅም የሚሰጣው ስደተኞች አሉ? ከሌላው ይበልጥ ተቀባይነት ያላቸው? አዎን ካሉ ለምን?

**There are many African and Arab refugees; the African refugees flee poverty and the Arab refugees flee the war raging in Iraq and Syria. With few exceptions, they are all left to themselves. A regime that does not care for its own citizens cannot develop a conclusive policy for refugees. In Algeria, the refugees owe their survival not to the State but to the generosity of the population. I do not think there is a selective support among Algerians. Religion forbids it. All people in distress are equal. However, the Arab refugees are less in difficulty than the African ones who are sometimes repatriated. This is not the case for the Syrians, while some of them, thanks to the language and to the pan-Arabist fraternal spirit, become integrated faster.**

ብዙ የአፍሪካ ኣና የአረብ ስደተኞች አሉ። የአፍሪካ ስደተኞች ድህነትን፣ የአረብ ስደተኞች ደግሞ፣ ኢራቅን እና ሶርያን እያናወጠ ያለውን ጦርነትን ሸሽተው ይሰደዳሉ። እጅግ በጣም ጥቂት ከሆኑት በስተቀር የቀሩት በሙሉ ነፍሳቸውን ለማዳን ነው የወጡት። ለራሱ ህዝብ ደንታ የሌለው መንግስት ጠቃሚ የሆነ መመሪያ ለስደተኞች ሊያወጣ አይችልም። በአልጀሪያ ስደተኞች መሰንበት የሚችሉት በመንግስት ሳይሆን በህዝቡ ለጋስነት ነው። በአልጀርያውያን ዘንድ መርጦ የመርዳት ነገር አለ ብዬ አላስብም። ኃይማኖት ይከለክላል። ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው። ያም ሆኖ የአረብ ስደተኞችን የሚገጥማቸው ችግር አንዳንዴ ተይዘው ወደ ሃገራቸው ከሚጋዙ የአፍሪካ ስደተኞች ያነሰ ነው። ይህ ሶርያውያንን አይመለከትም፡፡ ምክንያቱም፤ ለቋንቋ እና ለአረቦች ህብረት እና ወንድማማችነት መንፈስ ምስጋና ይግባውና፣ ጥቂቶቹ ወዲያውኑ ከህዝቡ ይዋሃዳሉ።

**Yasmina Khadra, Algeria / France, Pseudonym of Algerian writer Mohammed Moulessehoul**
ያስሚን ካድራ፣ አልጀሪያ / ፈረንሳይ፣ መሐመድ ሞልሶል፣ ያስሚን ካድራ በሚል የብዕር ስም የሚታወቅ ደራሲ፡፡

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.



# ARE THERE PRIVILEGED REFUGEES IN YOUR COUNTRY, I.E. REFUGEES THAT ARE MORE WELCOME THAN OTHERS? IF YES: WHY?

## በሀገርዎ ልዩ ጥቅም የሚሰጣው ስደተኞች አሉ? ከሌላው ይበልጥ ተቀባይነት ያላቸው? አዎን ካሉ ለምን?

**In almost every country, there are privileged refugees, and there always have been. Refugees, who bring treasures of qualifications with them, are not only welcome, but there are incentives for them. Rich countries are able to plunder the talents of other countries by attracting privileged refugees. In the era of enlightenment, in the 18th century, such practice was a sign of a minister's qualifications.**

በእያንዳንዱ ሀገር ማለት ይቻላል የበለጠ ተቀባይነት ያላቸው ስደተኞች አሉ፡፡ ነበሩም፡፡ ሃብት እና ሙያ ይዘው የሚመጡ ስደተኞች መልካም አቀባበል ብቻ አይደለም የሚደርግላቸው የማበረታቻ ስጦታዎችም አሏቸው። ሃብታም ሀገሮች ልዩ ስጦታ ያላቸውን የሌሎች ሀገሮችን ሰዎች በልዩ ተጠቃሚ ስደተኝነት ለመማረክ ይችላሉ። በ18ኛው ክፍለ የመገለጥ ዘመን እንዲህ አይነቱ ልምድ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሙብቃት ምልክት ተደርጎ ይታይ ነበር።

**Alexander Kluge, Germany,Writer, Film Maker and Producer.**
አሌክሳንደር ክሉገ፣ ጀርመን፣ደራሲ፣ ፊልም ሰራተኛ እና ፕሮዲውሰር

**Refugees with Christian background are more welcomed than Muslim refugees. Czechs believe Christian refugees are better prepared to assimilate in Czech culture and function within the rules of Czech society.**

ክርስቲያን ስደተኞች ከሙስሊም ስደተኞች የተሻለ ተቀባይነት አላቸው። ቼኮች ክርስቲያን ስደተኞች በቀላሉ ከህብረተሰቡ ጋር ለመቀላቀል፣ የቼክን ባህል ለመቀበል የቼክን ህዝቦች የአኗኗር መመሪያዎች ለመቀበል የተመቹ ናቸው ብለው ያምናሉ።

**Petra Hulovà, Czech Republic, Writer**
ፔትራ ሁሎቫ፣ ቼክ፣ ሪፐብሊክጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# IS FLIGHT FROM POVERTY LESS LEGITIMATE THAN FLIGHT FROM WAR OR POLITICAL OPPRESSION?

# በድህነት ምክንያት መሰደድ ተቀባይነቱ በጦርነት ወይም በፖለቲካ ጭቆና  ምክንያት ከመሰደድ ያነሰ ይሆን?

**What does the term ‘legitimacy’ imply? If that means intensity of a motivation to leave one´s home country, a legitimacy to claim a similarly difficult condition as persecuted ones, then yes. In that sense under certain circumstances poverty can be perceived as even more devastating than a persecution. Persecution with at the same time enough food to live on might be actually more liveable than extreme hunger with no persecution at all. However, if the ‘legitimacy’ of poverty implies a right to be unconditionally received in Europe, then I have to reply ‘no’ with all awareness of the tragic and dehumanising consequences.  Poverty as a sole reason should not automatically enable one to be unconditionally received in the EU, for there are unfortunately not unlimited resources to stick to such a practice unreservedly.**

ህጋዊ የሚለው ቃል እራሱ ምንን ነዉ የሚያመለክተው? የትውልድ ሃገርን ለመልቀቅ ያለውን ጫና ከባድነት የሚያመላክት ከሆነ፣ ከጥቃት ለማምለጥ ከሚሳደድ አይነት ሰው አስቸጋሪ ሁኔታ ጋር ከተነፃፃረ፣ አዎ ዝቅ ያለ ነው።  በዛው ልክ በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ ድህነት ከጥቃት ስጋት በከፋ ደረጃ ተቀባይ የሚሆንበት ጊዜ አለ። የከፋ ረሃብ  ለመኖር የሚያስችል በቂ ምግብ ካለው ሰው የጥቃት ስጋት ጋር ሲነፃፀር የከፋ ይሆናል። ሆኖም የድህነት ህጋዊነት ካለምንም ቅድመ ሁኔታ በአውሮፓ ተቀባይነት ማግኘት ከሆነ፣ መልሴ ድህነት የሚያስከትለውን ሰባዓዊ ውርደት፣ እና ሰቆቃ እየተረዳሁ እንኳ፣ አይሆንም ነው። ድህነት ብቻውን አንድን ሰው በአውሮፓ ህብረት ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ የለበትም። እንደ አለመታደል ሆኖም ይህን ለማድረግ የተትረፈረፈ የሀብት ምንጭ አለመኖሩ ግልፅ ነው።

**Petra Hulovà, Czech Republic, Writer**
ፔትራ ሁሎቫ፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# IS FLIGHT FROM POVERTY LESS LEGITIMATE THAN FLIGHT FROM WAR OR POLITICAL OPPRESSION?

## በድህነት ምክንያት መሰደድ ተቀባይነቱ በጦርነት ወይም በፖለቲካ ጭቆና  ምክንያት ከመሰደድ ያነሰ ይሆን?

**It's not less legitimate, but it is legally distinct. The refugee's status is defined by an urgent, immediate need for sanctuary: you become a refugee to save your life, whereas the economic migrant is considered to be voluntarily on the move with the aim of improving his or her life. It's striking how contradictory attitudes are to economic migrants: on the one hand, they're depicted as opportunists, self-seekers, and thus to be debarred from the privileges and rights of other self-seekers (those of us who live in incomparably richer circumstances). On the other hand, they're actively recruited as spare parts for our labour machine, as extra shifts to prop up economies threatened by stagnation or shrinking birth rates.**

ተገቢነቱ ያነሰ አይደለም። ሆኖም ግን ከህግ አንፃር ልዩነት አለው። የስደተኞች ሁኔታ በአንገብጋቢነቱ እና አስቸኳይ መጠጊያ ከማግኘት አንፃር ይታያል። ሕይወትህን ለማዳን ስደተኛ ትሆናለህ፣ ነገር ግን በድህነት መሰደድ የተሻለ ሕይወት ፍለጋ በፈቃደኝነት የሚደረግ ተደርጎ ይወሰዳል። ለኢኮኖሚ ስደተኞች ያለው አመለካከት እርስ በርሱ የሚጋጭ መሆኑ እራሱ በጣም አስደንጋጭ ነው። በአንድ በኩል ልክ ጥቅም አሳዳጆች፣ ራስ ወዳዶች  ተደርገው ይወሰዳሉ። በዚህ ሳቢያ እነዛ በንፅፅር የተሻለ ሕይወት የሚኖሩት ራስ ወዳዶች የሚያገኙትን ጥቅምና መብት እንዳያገኙ ይከለከላሉ። (ፍፁም ከእነሱ ጋር ሊነፃፀር በማይችል ደረጃ ካለነው እኛ)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለጉልበት ማሽኖቻችን እንደ መለዋወጫ፣ በውልደት ቁጥር መጠን መቀነስ ሳቢያ ባለበት የሚሄደውን መሻሻል የማያሳየውን ምጣኔ ሃብት ለመደገፍ ደግሞ እንደተጨማሪ አንቀሳቃሾች ይመለመላሉ፡፡

**Frances Stonor Saunders Great Britain, Historian and Writer.**
ፍራንሲስ ስቱነር ሳውንደርስ፣ ታላቋ ብሪታንያ፣ የታሪክ ባለሙያና ፀሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# IS FLIGHT FROM POVERTY LESS LEGITIMATE THAN FLIGHT FROM WAR OR POLITICAL OPPRESSION?

# በድህነት ምክንያት መሰደድ ተቀባይነቱ በጦርነት ወይም በፖለቲካ ጭቆና ምክንያት ከመሰደድ ያነሰ ይሆን?

**Escape from poverty is understandable but, in my opinion, cannot be equated with escape from war or political oppression. I think he who moves to another country to escape poverty fits the concept of immigrants, which should not be confused with the refugee status.**

ከድህነት የመሸሽን አስፈላጊነት ሊረዱት የሚችሉት ነገር ነው። በኔ አስተያየት ግን ከጦርነት ወይም ከፖለቲካዊ ጭቆና መሸሽ ጋር እኩል አይደለም። እንደማስበው ከድህነት ለማምለጥ ወደ ሌላ ሀገር የሚኮበልል ስደተኛ የሚለው ፅንሰ ኃሳብ ይመጥነዋል፡፡ ሽሽት ከሚለው ጋር መምታታት የለበትም።

**Milagros del Corral, Spain, Librarian**
ሚላግሮሰ ደ ኮራል፣ ስፔን፣ የቤተ መጻሕፍት ባለሙያ

**It is the contrary. Poverty is more dangerous than war or even political oppression. Poverty means the absence of life, to live in constant humiliation. To escape from it and to better one's situation is a very legitimate right.**

የለም እንዲያውም በተቃራኒው ነው። ድህነት ከጦርነት ይበልጥ፣ ከፖለቲካ ጭቆናም እንኳ ይበልጥ አደገኛ ነው። ድህነት ማለት ህይወት አልባ መሆን፣ በማያቋርጥ ውርደት ውስጥ መኖር ማለት ነው። ከዚህ ወደ ተሻለ ሁኔታ መሰደድ ማለት እጅግ በጣም ተገቢነት ያለው ነው።

**Amal Saqr, Iraq, Investigative journalist.**
አማል ሳቅር፣ ኢራቅ፣ መርማሪ ጋዜጠኛ

**Flight is always associated with the concept of „survival", be it poverty or war. The difference is that escaping poverty often is the result of a voluntary decision while escaping war almost always is the consequence of force. In most cases, this is also the basis for the difference between emigration and flight.**

ሽሽት ሁልጊዜም ቢሆን "መሰንበት" ከሚለው ፅንሰ ሃሳብ ጋር ይቆራኛል። ጦርነት ሆነ ድህነት። ልዩነቱ ድህነትን መሸሽ ብዙ ጊዜ በፈቃደኝነት የሚወሰን ውሳኔ ውጤት ነው። ከጦርነት የመሸሽ ሰበብ ብዙውን ጊዜ እጅግ አስገዳጅ ሁኔታ ነው፡፡ በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ በስደት እና ሽሽት መካከል ላለው ልዩነት መሰረቱ ይህ ነው።

**Petros Markaris, Greece, Writer and Translator**
ጴጥሮስ ማርካሪስ፣ ግሪክ፣ ጸሐፊና ተርጓሚ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# IS FLIGHT FROM POVERTY LESS LEGITIMATE THAN FLIGHT FROM WAR OR POLITICAL OPPRESSION?

## በድህነት ምክንያት መሰደድ ተቀባይነቱ በጦርነት ወይም በፖለቲካ ጭቆና ምክንያት ከመሰደድ ያነሰ ይሆን?

**If a refugee is a person who has nowhere to return to, it is not important why they had to leave in the first place. How can we measure the difference between the fear of bombs and the fear of hunger? Do we really dare to categorize terror hierarchically? And even if we did, what type of terror would be a better, more acceptable, option for us? Moreover, how do we measure what type of hope is greater and more legitimate? Is it the hope to find peace elsewhere; is it the one of a better and more useful life or the one of being saved from the persecution of raging political movements? Are we really in the position to claim that the need for safety is more important than the need for freedom? Making such hierarchical categorization is in fact the same as becoming an accomplice in crime.**

ስደተኛ ሰው ዞሮ መግቢያ የሌለው ከሆነ ገና ከመጀመሪያው አካባቢውን መልቀቁ አስፈላጊ አይደለም። በቦምብ መደብደብን መፍራትና እና ረሃብን በመፍራት መሃል ያለውን ልዩነት እንዴት ነው የምንለካው፡፡ እውን ሽብርን ደረጃ ልናወጣለት እንደፍራለን? እንደው አወጣንለት ብንል ምን አይነቱ ሽብር ነው ለእኛ የተሻለው? የተሻለ ተቀባይነት የሚኖረው? በተጨማሪም ምን አይነቱ ተስፋ ነው ከፍ ያለው እና ይበልጥ ህጋዊነት ያለው? ሌላ ቦታ ሰላም የማግኘት ተስፋ ነው? ሌላ ቦታ ሄዶ የተሻለ እና ጠቃሚ ህይወት መኖር ነው? ወይስ በአደገኛ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከመታረድ መዳን? በእርግጥ እኛ ደህንነትን ከመሻት ይልቅ ነፃነትን መሻት የበለጠ አስፈላጊ ነው ብለን ለመበየን የምንችልበት ሁኔታ ላይ ነን? ይህን አይነቱ የእርከን ክፍፍል መፍጠር ማለት በእርግጥ የወንጀሉ ተባባሪ መሆን ነው።

**Dubravka Stojanovic ,Serbia, Historian**
ዱብራቭካ ስታኖቪክ፣ ሰርቢያ፣ የታሪክ ምሁር

**A refugee is one whose existence is entirely "naked," "bare," ...**
ስደተኛ ማለት ህልውናው እንዳለ "እርቃኑን" የቀረ "ባዶ" ማለት ነው።...

**Eva Illouz, Israel, Writer**
ኢቫ ኢሎውዝ፣ እስራኤል፣ ጸሐፊ

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

© Nassim Rouchiche

# IS FLIGHT FROM POVERTY LESS LEGITIMATE THAN FLIGHT FROM WAR OR POLITICAL OPPRESSION?

# በድህነት ምክንያት መሰደድ ተቀባይነቱ በጦርነት ወይም በፖለቲካ ጭቆና  ምክንያት ከመሰደድ ያነሰ ይሆን?

**Not at all. The great migrations in previous centuries from Europe to America, Africa and Asia were primarily economically motivated. Former colonial powers certainly are not in a position to make a principle objection to economic refugees**

ጨርሶ ልዩነት የለውም። በቀደሙት ዘመናት የተካሄዱት ታላላቅ ስደቶች፣ ወደ አሜሪካ እና አፍሪካ፣ ዋና መነሻቸው ኢኮኖሚያዊ ነበር። የቀድሞ ቀኝ ገዢዎች በእርግጠኝነት በድህነት ምክንያት የሚሰደዱትን ለመቃወም መብት ሊኖራቸው አይችልም።

**Hans van den Brink, Netherland, Writer and Journalist**
ሃንስ ቫን ደ ብሪክ፣ ኔዘርላንድስ፣ ጸሐፊና ጋዜጠኛ

**Poverty is the consequence of economic disorganization, most of the time caused by corruption and the concentration of profit in the hands of a few. The poorer a country's population is, the less access they have to education, health care, public local transport and recreation, and the more they suffer from violence. In some countries, everyday violence in the cities or in the countryside kills more people than are currently killed by numerous wars, and continuous hardship as well as poor education are instruments of political suppression.**

ድህነት የተቃወሰ ኢኮኖሚ ውጤት ነው። አብዛኛውን ጊዜ በሙስና እና ሃብት በጥቂቶች እጅ መከማቸት ሳቢያ የሚፈጠር ነው። የአንድ ሀገር ህዝብ ደሃ በሆነ ቁጥር ትምህርትን፣ የጤና ተቋማትን፣ መጓጓዣን ለመጠቀምና እና ለመዝናናት ያላቸው እድል አነስተኛ ነው፡፡ ይበልጥ ደግሞ በግጭቶች ይጎዳሉ። በአንዳንድ ሀገሮች በከተሞች እና በገጠር በግጭቶች ምክንያት በየቀኑ የሚሞተው ሰው ቁጥር፣ ዛሬ በተለያዩ ጦርነቶች ከሚሞተው ሰው ቁጥር ይበልጣል። በዛ ላይ የማያቋርጥ የኑሮ ፈተና  ከትምህርት እጦት ጋር የፖለቲካ ጭቆና መሳሪያዎች ናቸው።

**Luiz Ruffato, Brasil, Writer**
ሉዊዝ ሩፋቶ፣ ብራዚል፣ ጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# IS FLIGHT FROM POVERTY LESS LEGITIMATE THAN FLIGHT FROM WAR OR POLITICAL OPPRESSION?

## በድህንት ምክንያት መሰደድ ተቀባይነቱ በጦርነት ወይም በፖለቲካ ጭቆና  ምክንያት ከመሰደድ ያነሰ ይሆን?

**Not at all. The great migrations in previous centuries from Europe to America, Africa and Asia were primarily economically motivated. Former colonial powers certainly are not in a position to make a principle objection to economic refugees**

ጨርሶ ልዩነት የለውም። በቀደሙት ዘመናት የተካሄዱት ታላላቅ ስደቶች፣ ወደ አሜሪካ እና አፍሪካ፣ ዋና መነሻቸው ኢኮኖሚያዊ ነበር። የቀድሞ ቀኝ ገዢዎች በእርግጠኝነት በድህነት ምክንያት የሚሰደዱትን ለመቃወም መብት ሊኖራቸው አይችልም።

**Hans van den Brink, Netherland, Writer and Journalist**
ሃንስ ቫን ደ ብሪክ፣ ኔዘርላንድስ፣ ጸሐፊና ጋዜጠኛ


**Poverty is the consequence of economic disorganization, most of the time caused by corruption and the concentration of profit in the hands of a few. The poorer a country's population is, the less access they have to education, health care, public local transport and recreation, and the more they suffer from violence. In some countries, everyday violence in the cities or in the countryside kills more people than are currently killed by numerous wars, and continuous hardship as well as poor education are instruments of political suppression.**

ድህነት የተቃወሰ ኢኮኖሚ ውጤት ነው። አብዛኛውን ጊዜ በሙስና እና ሃብት በጥቂቶች እጅ መከማቸት ሳቢያ የሚፈጠር ነው። የአንድ ሀገር ህዝብ ደሃ በሆነ ቁጥር ትምህርትን፣ የጤና ተቋማትን፣ መጓጓዣን ለመጠቀምና እና ለመዝናናት ያላቸው እድል አነስተኛ ነው፡፡ ይበልጥ ደግሞ በግጭቶች ይጎዳሉ። በአንዳንድ ሀገሮች በከተሞች አና በገጠር በግጭቶች ምክንያት በየቀኑ የሚሞተው ሰው ቁጥር፣ ዛሬ በተለያዩ ጦርነቶች ከሚሞተው ሰው ቁጥር ይበልጣል። በዛ ላይ የማያቋርጥ የኑሮ ፈተና  ከትምህርት እጦት ጋር የፖለቲካ ጭቆና መሳሪያዎች ናቸው።

**Luiz Ruffato, Brasil, Writer**
ሉዊዝ ሩፋቶ፣ ብራዚል፣ ጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.



# DO REFUGEES IN YOUR COUNTRY RECEIVE FAIR TREATMENT?

# በናንተ ሀገር ስደተኞች ተገቢው መስተንግዶ ይደረግላቸዋል?

**No. Even when they get a permit with a lot of effort, a mafia of subcontractors will gamble on the quota of funds granted for their livelihood.**

በፍፁም። በስንት መከራ እና ጣጣ መኖሪያ ፍቃድ ቢያገኙም እንኳ፣ ለመኖሪያቸው በሚመደብላቸው የገንዘብ ድርሻ፣ ኮታ ላይ የማፍያ ተወካዮች ቁማር ይጫወቱበታል።

**Erri de Luca, Italy, Writer**
ኤሪ ደ ሉቻ፣ ጣሊያን፣ ፀሐፊ

**No. Refugees in Finland rarely end up on the street; we are able to accommodate them, but people don't want anything to do with them. Especially problematic was the deportation of refugees in the summer of 2016, to countries in which the danger of being persecuted or killed is especially high.**

አይደረግላቸውም። ፊንላንድ ውስጥ ስደተኞች መንገድ ላይ የሚታዩት አልፎ አልፎ ነው፡፡ ልናስተናግዳቸው አቅሙ አለን፤ ነገር ግን ህዝቡ ከነሱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ማድረግ አይፈልግም። በተለይ አሳፋሪው ድርጊት የተፈጠረው በ2016 በጋ ላይ ነበር፡፡ ስደቶኞች ጥቃት ሊደርስባቸው ወይም ሊገደሉ የሚችሉበት ሁኔታ ከፍተኛ ወደሆነባቸው ሃገራት ተገደው እንዲመለሱ ሲደረግ።

**Sirpa Kähkönen, Finland, Autorin und Kolumnistin**
ሲርፓ ኬህኮነን፣ ፊንላንድ፣ ደራሲና ዓምደኛ

GOETHE INSTITUT

Sprache. Kultur. Deutschland.

© Nassim Rouchiche



# DO REFUGEES IN YOUR COUNTRY RECEIVE FAIR TREATMENT?

## በናንተ ሀገር ስደተኞች ተገቢው መስተንግዶ ይደረግላቸዋል?

No. Not at all. The Hungarian government tries to present a negative image of refugees. Xenophobic and inhumane. For a year or even more, refugees have been depicted on posters as enemies;  And in the meantime, even Hungarians have become "economic refugees" everywhere in Europe. Employees such as nurses, teachers, physicians, bricklayers, waiters, computer scientists, cleaning ladies, prostitutes. Most families raise their children according to the motto: „Get away from here." "Go abroad". "Flee."

እረ በጭራሽ! የሀንጋሪ መንግስት የስደተኞችን መጥፎ ገፅታ ብቻ ለማሳየት ነው የሚሞክረው። የውጭ ዜጎች ጥላቻ እና ኢሰብአዊ ድርጊት።  ለዓመት ከዛም ለበለጠ ግዜ ስደተኞች በፖስተሮች ላይ ምስላቸው ልክ እንደ ጠላት ተደርጎ ነበር የሚወጣው። በአሁኑ ጊዜ ሀንጋሪያን ራሳቸው እንኳ የኢኮኖሚ ስደተኞች ናቸው። በአውሮፓ በየቦታው በነርስነት፣ በመምህርነት፣ በሀኪምነት፣ በግምበኝነት፣  በአስተናጋጅነት፣  በኮምፒዩተር  ባለሙያነት፣  በፅዳት  ሰራተኝነት  እና  በሴተኛ አዳሪነት ስራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ብዙ ቤተሰብ ልጆቹን " ከዚህ ውልቅ በል" "ተሰደድ" "ሽሽ" በሚል መሪ ቃል ነው የሚያሳድገው።

**Hungary, Noémi Kiss, Writer**
ኖኤሚ፣ ኪስ፣ ሃንጋሪ፣ ጸሐፊ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.



# DO YOU THINK THAT THE NUMBER OF REFUGEES A SOCIETY CAN ABSORB IS LIMITED?

## ማህበረሰብ መቀበል የሚችለው የስደተኛ ቁጥር የተወሰነ መሆን አለበት?

**No. Because society doesn't have the right to decide who gets to be part of society. We are all part of society, whether society likes it or not. By existing we are integrated / assimilated into the world of the living.**

የለበትም። ምክንያቱም ማህበረሰብ ራሱ ማን የማህበረሰቡ አካል እንደሚሆን የመወሰን መብት የለውም። ማህበረሰቡ ወደደም ጠላም፣ ሁላችንም የማህበረሰቡ አካላት ነን። በመኖራችን/በመከሰታችን ብቻ ከህያዋን ዓለም ጋር ተዋህደናል፣ ተቀላቅለናል።

**Aman Sethi, India, Journalist and Writer.**
አማን ሴቲ፣ህንድ፣ጋዜጠኛና ጸሐፊ

**No, of course not. Nevertheless, when we speak about the refugee situation in Europe, we are speaking of more than 500 million people who refuse to accept two, three or four million. This is a disgrace. Europe fails the first test.**

ኧረ በጭራሽ። በአውሮፓ ስላሉ ስደተኞች ሁኔታ ስናወራ 500 ሚሊዮን ሰዎች ሁለት፣ ሶስት እና አራት ሚሊዮን ሰዎችን አናስጠጋም ስለማለታችን ነው። ይህ ውርደት ነው። አውሮፓ የመጀመሪያውን ፈተና ወደቀች።

**Harald Welzer, Germany, Sociologist**
ሃራልድ ቬልሰር፣ ጀርመን፣ ሶሺሎጂስት

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

# DO REFUGEES IN YOUR COUNTRY RECEIVE FAIR TREATMENT?

# በናንተ ሀገር ስደተኞች ተገቢው መስተንግዶ ይደረግላቸዋል?

**The right of asylum is boundless and has no quotas. Tiny Lebanon welcomes more than one million Syrians, and so does tiny Jordan. You should know that only a very small number of people wish to leave their geographical area, look for another continent. Only 5% of world refugees will take upon themselves asylum requests in faraway countries. These are reasonable quotas European nations can easily meet.**

ጥገኝነት የማግኘት መብት ገደብ የለሽና ኮታ የሌለው ነው። ሚጢጢዋ ሊባኖስ ከሚሊዮን በላይ ሶርያውያንን አስተናግዳለች። ሚጢጥየዋ ዮርዳኖስም እንዲሁ። የሚኖሩበትን አካባቢ ትተው ወደ ሌሎች አህጉራት የሚሰደዱት በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ መሆናቸውን ማወቅ አለባችሁ ፡ ፡ በዓለም ላይ 5 ከመቶ የሚሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው ከተወለዱበት አካባቢ በጣም ርቀው ሄደው ጥገኝነት የሚጠይቁት። ይህ ደግሞ የአውሮፓ መንግስታት በቀላሉ ሊያስተናግዱት የሚችል ቁጥር ነው።

**Erri de Luca, Italy, Writer**
ኤሪ ደ ሉቻ፣ ጣሊያን፣ ፀሐፊ

**No society has never burst because too many people have been absorbed. Society is a seamless thing. It grows and shrinks and morphs and expands.**

አንድም ማህበረሰብ ብዙ ሰዎችን ስለተቀበለ ሲፈነዳ አልታየም። ማህበረሰብ ለከት የሌለው ነገር ነው። ያድጋል፣ ይመናመናል፣ ይስፋፋል፣ ይለወጣል።

**Ruwanthie de Chickera, Sri Lanka, Theatre and Film producer**
ሩዋንቲ ዴ ቺከራ፣ ሲሪላንካ፣ የቲያትርና ፊልም አዘጋጅ

© Nassim Rouchiche

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.